www.xtrapapers.com

M12/1/A1AMH/HP1/AMH/TZ0/XX

22120013

International Baccalaureate®
Baccalauréat International
Bachillerato Internacional

**AMHARIC A1 – HIGHER LEVEL – PAPER 1**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU SUPÉRIEUR – ÉPREUVE 1**
**AMHÁRICO A1 – NIVEL SUPERIOR – PRUEBA 1**

Thursday 10 May 2012 (morning)
Jeudi 10 mai 2012 (matin)
Jueves 10 de mayo de 2012 (mañana)

2 hours / 2 heures / 2 horas

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a commentary on one passage only.
- The maximum mark for this examination paper is *[25 marks]*.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Rédigez un commentaire sur un seul des passages.
- Le nombre maximum de points pour cette épreuve d'examen est *[25 points]*.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un comentario sobre un solo fragmento.
- La puntuación máxima para esta prueba de examen es *[25 puntos]*.


© International Baccalaureate Organization 2012

www.xtrapapers.com



*ከሚከተሉት ምንባቦች አንዱን መርጠህ አስተያየት ስጥ(ስጭ)።*

**1.**

እንደዚህ በመማርና በማስተማር ስናወካ ከቆ§ን በኋላ በድንገት እንኮዩ አብሽሬ እየሮጠች መጣች@ "ዝም በሉ ወሂዱ ተዚህ ተነሡ በቃ" አለች አባረረችን። ሁላችንም ደነገጥንና ተበታተንን@ እኔ ግን መቼም አላርፍም የሆነውን ነገር ለማወቅ ያንጊዜውኑ ሮጥኩና እልፍኝ ገባሁ።

መጋረጃ ተጥሎ እመይቴ ያቃስታሉ። ከወደ ጀርባ ዞርኩና ወደ እመይቴ ተጠጋሁ።ከመሬት በላይ ከፍ አድርገው አስቀምጠዋቸዋል። እግሮቻቸውን እንፈራጠው ጋለል ብለው ተደግፈዋል። ምጥ ይዟቸዋል። አንዲት የአደሬ ሴት (ስሟ ተዘነጋኝ ቡሽሮ ነው ይመስለኛል) አዋላጃቸው ነች ተብላ አለቃ ሀብተ ማርያም አስመጥተዋል@ ከመይቴ እግሮች ሥር ተቀምጣለች ትጠባበቃለች።

ሴቶቹ ከመጋረጃ ግቢ ሲያገኙኝ ጊዜ& የተመዘዘ ካራ ሰጡኝ@ ከእመይቴ ራስጌ አቆሙኝ@ እንደዚህ የጎራውን ደንደስ ከጫንቃዬ ላይ አስደግፌ እጠባበቃለሁ። ሴቶቹ ያማጥናሉ "ማርያም ማርያም" ይላሉ። እኔም እንደነሱ ልመናዬን አፋጠንኩ።

ምጡ እመይቴን አልጎዳቸውም@ ሴቶቹ ማማጠናቸውን ተውና ድምፃቸውን በጣም ዝቅ አድርገው ተንሾካሾኩ@ ልጅ መወለዱን በመላ ዐወቅሁ። ነገር ግን ድምፁን አልሰማሁትም@ አዲስ የተወለደውን ልጅ ወደ ጓዳ ያሸሹት መሰለኝ። አለቃ ሀብተ ማሪያም ወደ ጓዳው ውስጥ እየገቡ እየወጡ እየተመላለሱ ከሴቶቹ ጋር ይነጋገራሉ።በኃላ ልጁን ወዴት እንዳደረሱት ለማወቅ አልተቻለኝም። እደዚህ እመይቴ ተገላግለው ጥሬ ቅቤ ከራሳው ላይ በጉሎ ቅጠል ለጠፉላቸው።

እመይቴ ውሃ ለመኑ። "እባካችሁ ውሃ ስጡኝ" አሉ። አለቃ ሀብተ ማርያም ወተት እንዲሰጧቸው አዘዙ። ወተቱን በቀመሱ ጊዜ እመይቴ ተቆጡ "በጦም አስገደፋችሁኝ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ይወዱላችኋል?" እያሉ አማረሩ። አለቃ ሀብተ ማሪያም ቄሶች አስገቡና እግዚአብሔር ይፍታ አሰኙተው "ንስሐ በኋላ መቀበል ነው እንጂ ምንም ኋጢአት የለበትም" እያሉ አጽናኗቸው።

ውድቅት ዐለፈ፤ የእንግዴ ልጅ አልወርድ ብሎ አስቸገረ። ማታ የተገላገሉ ከዶሮ ጩኸት በኋላ እንኳ ሳይወረድላቸው ቆየባቸው። ሊነጋጋ አቅራቢያ ተዳከሙ መናገር ያቅታቸው ጀምር ፤ ሰውነታቸው መጣም ወፍሮ ነበርና ጉዳት በዛባቸው። እየቆዩ ብቻ አንዳንድ ጊዜ ይናገራሉ። "ãረ ሞትኩ ያቡነ ተክለ ሃይማኖት ያለህ" ይላሉ። ሴቶቹ ሁሉ ተጨነቁ ያለቅሳሉ እኔም እንቅልፍና ድካም አልተሰሙኝም።

አለቃ ሀብተ ማርያም ትእዛዝ ሰጡ። አዋላጅዋ እጅዋን ትታጠብና ጣቶችዋን እስገብታ ቀስ ብላ የእንግዴ ልጁን ወደ ውጪ እየሳበች ታስወጣው፤ ብለው አልጎመጎሙ። ሴቶቹ ይህን በሰሙ ጊዜ ፊታቸውን አኮማተሩ ለቅሶም አበረቱ።

አዋላጅዋ እንደታዘዘችው አደረገች እመይቴ ክፉኛ ተንሰቀሰቁ፤ ዲምፃቸው ልቤን ነካው፤ የባሰውን እንባዬ ፈሰሰ።

እመይቴ ጮሁ "ãረ ገደላችሁኝ& እባንችሁ ስለ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጥቂት አስተንፍሱኝ@ ምነው ጨከናችሁብኝ! ምን አልኳችሁ?..."

አዋላጅዋ ፋታ አልሰጠቻቸውም ዝም ብላ ትጎለጉላለች@ እመይቴ ተዳከሙ ተዝለፈለፉ በዙሪያቸው ደጋፊች በዙ:: ሊነጋ ነው ወፎች መንጫጫት ጀመሩ ጭለማው ሊገፍ ነው ጧት በማለዳ እመይቴ ዐረፉ::

ከዚህ ቀን በኃላ አለቃ ሀብተ ማርያምን ሳያቸው የእናቴ ገዳይ ይስሉኛል:: ገና በሩቁ ሳያቸው ደሜ የፈላብኛል:: ላነጋግራቸው አልቻልኩም@ ከንቱ ሰው ይመስሉኝ ነበር:: (ከአውሮፓ ከተመለስኩ በኋላ እንኳ ይህ ስሜት አልተወኝም::)

ተክለ ሀዋርያት ተክለ ማርያም፣ ኦቶባዮግራፊ (የህይወቴ ታሪክ) ፣አ.አ.ዩ ማተሚያ ቤት፣(1998)::



www.xtrapapers.com

www.xtrapapers.com



**2.**

ካስማና ማገሩ እየተለያየ
ምሰሶው አዝምሞ… ጎጆ እየፈረሰ
ከጨቅሎች ጉንጭ ላይ…
ሀዘን ያጠለለው… እንባ እየታፈሰ
መጥኔ ሲያሰኝ ቀኑ… "ዋኔ ዋኔ" ስንል
በኤሎሄ ሲቃ… ዋይታን ስንቃጠል
የት ገባች ራሄል?!
ራማ ላይ ቆማ-እሪ እንዳትልልን?

ባበሻ አጉል ፈሊጥ… እድል ስትመተር
"ልጅ በእድሉ ያድጋል"… ተብለን ስንፈጠር
መራብ & መጠማቱ… መታረዝ ሳያንሰን
በሽታ ሰይፍ ይዞ… ሺ-ቦታ ሲቆርጠን
ቀስፎ& ሰንጎ… ትኩስ ደም ሲያስተፋን
የት ገባች ራሄል… እሪ እንዳትልልን?
በእፍኝ ምድር ላይ
እንዲህ ስንለያይ
ድሎት ከፊታቸው…
በእኩዮቻችን - ግንባር እያበራ
ሲስቅ & ሲፍለቀለቅ… ሲጨፍር ዳንኪራ@
በተደለደለው…ጎዳና ተራምደው
የእውቀት ታንኳ ላይ… ሲጓዙ ተሳፍረው
የት ገባች ራሄል… እንዳትጠይቅልን
እንባዋን ረጭታ… እንዳትዘክረን?!

www.xtrapapers.com



አያምርብን ይሆን ... እርሳስ መጨበጡ
ይገደንስ ይሁን... ወረቀት መግለጡ
ከፊደል ገበታ... ከስር መቀመጡ???
'ሀ - ሁ' ብሎ መቁጠር... 'በ' ና 'ቡ' ን ማገበቡ
'ፐ - ፑ ' ብሎ መዝለቅ... 'ለ' ና 'ሉ' ን መጻፉ
ከታችኛው ክፍል... ወደ ላይ ማለፉ???
አይሆንልን ይሆን ...
እምር ብንራመድ... ብርሃን ቢመራን?!
ጨለማው ከብዶብን - አልነጋ ሲል ሌቱ
የሞት ጣር አጥልቶ - ሲያስፈራ ሰዓቱ
በቀቢጸ ተስፋ - ጭብጥ& ኩርምት ብለን
ቁር በስል ጥፍሮቹ - ደጋግሞ ሲፍረን
እንጎርሰው ስናጣ!!
ቆዳና አጥንታችን - አንድነት ሲጣበቅ
እንለብሰው ሳይኖር
ገላ ክብሩን ሲያጣ - ነፍስ ስትሰቀቅ
የት ገባች ራሄል ሳታደርስ አደራ
ልሳን ሳታበድር - ብጤዋን ሳትጠራ?!
ላንጸድቅ... ተተክለን
ላንበቅል... ተዘርተን
ዛሬን ጭጋግ ወርሶት... ሲመክን ነጋችን
ተስፋ ሲጠልበት... ሲጠቁር ቀናችን
የት ገባች ራሄል?!
የእልፎች አንደበት... የሚሊዮኖች ቃል::

አንዱአለም አባተ፣ "የት ገባች ራሄል?!"፣ የረዘመ ትንፋሽ፣ፋር ኢስት ትሬዲንግ ፣(2000)::